# ዘመቻ ጴጥሮስ
## ዳግም አስቸኳይ ወገናዊ ጥሪ!

የኢትዮጵያ ህዝብ በመከራ ሲፈተን፤ሲበደል፤ ፍትህ ሲጓደልበት ድምፃቸውን ያሰሙ የነበሩ የኃይማኖት አባቶች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ከህዝቤ ውርደት በፊት እኔን ብለው አንገታቸውን ይሰጡ የነበሩ መንፈሳዊ አባቶች እንደነበሩን በታሪክ ሲጠቀስ ይኖራል። ዛሬ ላይ ቆሞ ለሚያስተውለውና ለሚረዳው ሀገራችን ከጠላት ወረራ ወዲህ እንደዚህ ጊዜ በጠላቶቿ የተጠላለፈ ጥቃት ውስጥ አልገባችም። በመሆኑም ከምንም ጊዜ በበለጠ ህዝቡ አንድነቱን ጠብቆ፣ተባብሮ፣ የሃገሩን ጠላቶች እንዲመክት፤ መክሮና ዘክሮ ለሀገሩ ብሔራዊ ጥቅም እንዲሠራ፤ ማድረግ ከኃይማኖት አባቶች የሚጠበቅ ቅዱስ ተግባር ነበር።ነውም።

ዛሬ ታድያ ያ ሁሉ ቀርቶ ትናንት ንጹሃን ኢትዮጵያውያንን በበደኖ፣በወተር፣በአሰቦት፣ በአርባጉጉ፣ በአርሲ፣ ከነነፍሳቸው በገደል እየወረወረ ፊልም ይቀርፅ ከነበረው ወያኔ ጋር፤ ትናንት በየካቲት 12 አደባባይ ኤርትራ ኢትዮጵያዊ ናት ያሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ወጣት ኢትዮጵያውያንን በታንክ ከጨፈለቀው ወያኔ ጋር፤ ትናንት በጎንደር አደባባይ እየሱስ ሃይማኖታችን ይጠበቅ ያሉ ክርስቲያናትን ከጨፈጨፈው ወያኔ፤ በጌዲኦ በጉጂ፣ በጂማ በሊሙ፣ በአሰንዳቦ፣ በሊሙ ሰቃ ክርስቲያናት እንዲታረዱ ካደረገው ወያኔ፤ የባለ አራቷ ወደቦች ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያን ያለወደብ አስቀርቶ ዛሬ የነ ፖርት ሱዳን፣ሞምባሳ፤ጂቡቲና መንግስት የሌላት ፑንትላንድ ገባር ካደረጋት ወያኔ ጋር፤ ህዝባችንን ከሃብትና ከመሬቱ ነቅሎ ኢትዮጵያን የባዕዳን ሃብት ካደረጋት ወያኔ ጋር፤ ዛሬም ህዝባችንን በጎሳና በቋንቋ ከፋፍሎና ለያይቶ እርስ በእርሱ ከሚያባላን ወያኔ ጋር በመሆን ለውርደቱ የጵጵስና ቆብና ለርፍራፊ ጥቅማ ጥቅም ሲባል ያከበራቼውን ህዝብ በመናቅና በማዋረድ ከጠላት ጋር በማበር የኢትዮጵያ ህዝብ የመከራ ዘመን እንዲጨምር የወያኔ ዕድሜ እንዲረዝም የሚሠሩት ካኅናት ቁጥር እየጨመረ ነው።

ይህ ደግሞ ያለምክንያት አልተከናወነም። እንደሚታወቀው በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ካቋቋሟቼው የተለያዩ ተቋማት ሁሉ አብያተክርቲያናት ሠፊውን ስደተኛ በማሰባሰብ በኩል ጉልህ የሆነ አስተዋፃኦ አላቸው። በእነዚህ አብያተክርስቲያናት የሚሰባሰበውን ኢትዮጵያዊ ስለሀገሩ እንዲጨነቀው፣ ያገባኛል ብሎ ተሳታፊ እንዲሆንና ያቅሙን እንዲያደርግ በአንዳንዶቹ አብያተክርስቲያናት እንደሚደረገው በአብዛኞቹ የሚደረግ ቢሆን የመከራችን እድሜ ፈጥኖ እንዲያጥር ሊጫወት የሚችለው ሚና ቀላል አልነበረም። በዚህ በኩል የወያኔው ቡድን የማይናቅ ሥራን በመሥራቱ እነሆ ዛሬ የኢትዮጵያን ጉዳይ አንስቶ በቤተክርስቲያን መነጋገር ውጉዝ ከማሪዮስ ሆኖ እነርሱ የሚሠሩት፣የሚውሉት፤ መመሪያና ሹመት መሬትና ጵጵስና የሚያገኙት ከወያኔ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያውያን ግን የሃገራችንን ጉዳይ በምንሰባሰብበት ቤተክርስቲያን እንዳናነሳ "ፖለቲካና ኮረንቲ" ወይም "የቄሳርን ለቄሳር" እየተባልን በሃይማኖት ስም እየተደፈቅን "እርሱ ያመጣውን እርሱ እስኪመልሰው" ወይም "እርሱ የቀባውን ሰው አያወርደውም" እየተባልን ብቻ እንደእንስሳዋ ያገኜነውን ተመግበን በዚሁ ስደታችን እንድንኖር እያመቻቹን ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ የመስዋዕትነት ገድለ ታሪክ ያሸበረቀው የነአቡነ ጴጥሮስ የአቡነ ሚካኤል እና የአራት ዓይናማዎቹ አገርና የሌሎችም ሃይማኖታዊ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን የዕምነት ቤቶች እነአባ መላኩን በመሳሰሉ ጮሌና ሆድ አደር ከሃዲ አባት ተብዬዎች እየተመሰቃቀለ ነው። እምነት ቤቱ ከመንፈሳዊ ዕምነትና ሀገራዊ እሴትነቱ ይልቅ የወያኔነት መመልመያና ማስገበሪያ እየሆነ ነው። አባ መላኩ ወያኔ ፈለጠኝ ቆረጠኝ ወደ ሃገሬ ብመለስ ያሥረኛል፤ ይገድለኛል፤ ብለው የአሜሪካንን መንግሥት ዋሽተው የመኖሪያ ፈቃድ ያወጡና ጊዜውን ጠብቀው የአሜሪካ ዜግነትን የወሰዱ ናቸው። ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ከሃገር ወዳዱ ስደተኛ ጋር አጋር መስለው በመቆም የወያኔን አስተዳደር ሲያወግዙና እንዲያውም እነዚህ " ምናምንቴዎች " እያሉ ወያኔዎችን ሲያጣጥሉ ቆይተው በኋላ የአባ ጳውሎስ የጥቅም ሰለባ በመሆን በጵጵስና ቆብ ተሸጠው ምነዋ አባ ሲባሉ " የእኔ ሬሣ እንደ ስደተኛው በሳጥን ወደ ኢትዮጵያ አይላክም " በማለት አዲስ አበባ ከአባ ገብረመድህን የጵጵስና ቆብ ተቀብለው ለአዋሳ ሃገረ ስብከት ተሾመው ነበር።

እነአባ መላኩ ዛሬ በድፍረትና በንቀት ኢትዮጵያን ከሚያዋርዱት ጎጠኞችና ከፋፋዮች ጋራ ተሰልፈው እየሰሩ ናቸው።ህዝባችን የጎጠኞቹ መከራ ያነሰው ይመስል እነዚህ ደግሞ በበኩላቸው ከቦታ ቦታ ከቤተክህነት ቤተክህነት እየለዋወጡ የጎጠኞችና ከፋፋዮች መሣሪያ ሆነው ህዝባችንን ቁም ስቅል ያሳዩታል። ይከፋፍሉታል። ይህ ሁሉ ደባ፣ ተንኮል፣ ክዳት፣ ድፍረትና ንቀት ኢትዮጵያ ውስጥ አፉን በአጋዚ ጦር በተለጎመው ህዝባችን ቢሆን ኖሮ ላይገርመን ይችል ነበር።

የሚያስገርመው  ግን ይህ ሁሉ የሚፈፀመው ነፃ ነን በምንለውና ብዙ እናውቃለን በምንለው ውጭ ሃገር በምንኖረው ኢትዮጵያዊያን ላይ መሆኑ ነው በሽታው። ሀገር ቤት በኢጋዚ ቁጥጥር ሥር ያለው ህዝብማ የመጣብኝን እጋፈጣለሁ ብሎ አባ መላኩን አባ ጳውሎስ ከነሰጣቼው ቆብ በጀግንነት አባርሯቼዋል።ከአዋሳ ከተባረሩ በኋላ ነው እንግዴህ አብዛኞቻችንን ያሰደደው ጎጠኛ አስተዳደር ለእኛው ለስደተኞቹ “መንፈሳዊ ህይወት” ጠባቂ አስተዳዳሪ እንዲሆኑ የወያኔ የሰሜን አሜሪካ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አድርጎ በመሾም የላካቸው። መጥተውም አላረፉልንም። ይሄው በዋሽንግተንና አካባቢ የሚገኙትን አብያተክርስቲያናት ሁሉ ለወያኔ ገባሪ እንዲሆኑ እየሠሩ ነው። ባለፈው ሁለት ሳምንትም ሁሉም እንደሰማው ያረፉበትን የደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የወያኔው ፓትሪያሪክ ረዳት የሆኑትን አባ ገሪማን እማኝ አድርገው ስደተኛው አፈር በልቶ በላቡና በጉልበቱ የገዛውን ቤተ ክርስቲያን ”ይህ ቤተ ክርስቲያን ከዛሬ ጀምሮ በአባ ገብረመድህን (አባ ጳውሎስ) አስተዳደር ሥር የገባ መሆኑን እንድታውቁት” በማለት ያለምንም ተጨማሪ ማብራሪያ በድፍረትና በንቀት ለምዕመኑ ገልፀዋል።

በኛ በኩል መሠረታዊ የሆነውን የወያኔን ደባና የአባ መላኩን ጥጋብ እንዲሁም ወያኔ በየአብያተክርስቲያናት ያጠመደውን አሽክላ ለአንዴና ለሁሌም መበጣጠስ አለብን ብለን ነው ይንንን የተቀደሰ ያልነውን ዘመቻ በአርበኛው አቡነ ጴጥሮስ ስም የጀመርነው።

በዚህ መሠረት የዘመቻ ሥራችንን እ.አ.አ. እሁድ ፌብሯሪ 26 ቀን 2012 በደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት በርካቶቻችን ወጥተን የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ የጀመርን ሲሆን በዚሁ ዕለት አባ መላኩ፤

ሀ/ እዚያው ቤተክርስቲያን እንዳይውሉና ከቤተክርስቲያኑ በመሸሸ ቨርጂኒያ በምትገኘው ኪዳነምኅረት ቤተክርስቲያን እንዲውሉ አድርገናቸዋል።

ለ/ በስደተኛው ላብ የተቋቋመውን ካንሳስ ሲቲ የሚገኘውን የካንሳስ ኪዳነ ምኅረትን ቤተ ክርስቲያን በሌላው ከሃዲና አዲስ ሹመኛ ሊቀ ካኅናት አባ ተስፋ አማካኝነት ለመረከብ ወደ ካንሳስ ሲቲ እንደሚሄዱ ይፋ ካደረጉ በኋላ በሁላችሁ ትብብር ጉዟቸውን እንዲሰርዙ አድርገናል።

ዘመቻችንን በመቀጠል አሁንም ከሚቀጥለው እሁድ ማርች 4 ቀን 2012 ጀምሮ አባ መላኩ ከዚህ እስከተወገዱበት ዕለት ድረስ በየሳምንቱ እሁድ የተቃውሞ ሰልፋችን በደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በር ላይ ይቀጥላል። ይህ ብቻ አይደለም አባ መላኩ በሚሄዱበት ማንኛውም የዋሽንግተንና አካባቢው ቤተክርስቲያን ሁሉ በመገኘት በአባ መላኩ ላይ ተቃውሞአችንን እናሰማለን። ይህንንም ሁሉም አብያተክርስቲያናት ከወዲሁ እንዲያውቁልን አበክረን እንገልፃለን።ውድ ሀገር ወዳድና ሃይማኖታችሁን አፍቃሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ ሀገርን ከጥፋት ህዝብን ከዕልቂት ለማዳን የመጀመሪያው ሥራችን መሆን የሚገባው የኛ አንድነት ነው። የኛ አንድነት ደግሞ ከሃዲዎችን በጉያችን አቅፈን የሚሆን አይደለምና በእውን ፀር-ወያኔ ከሆን፤ የየግል አመለካከቶችና ጉንጭ አልፋ ፍልስፍናዎችን **ለጊዜ** ትተን በዚህ የፀረ-ከሃዲዎች አንቅስቃሴ በመሳተፍ ወገናዊ አደራችንን እንወጣ። ጠላታችን **ፍርሃትና** ያነቀዘን **አለመተማመን** በዚሁ ይሠበሩ።

**ስለዚህ በዚህ ታላቅ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ማንኛውም በአካባቢው የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቦታው እንዲገኝልን። ይህንን መልዕክት ያገኛችሁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዋሽንግተንና አካባቢው ለሚገኙ ዘመድ ወዳጅ ጓደኞቻችሁ በሙሉ ስልክ በመደወልና ኢሜል በማድረግ በተቃውሞ ሰልፋችን ላይ እንዲገኙ እንድታደርጉልን በግፈኞች መዳፍ ሥር በሚማቅቀው ህዝብ ስም እንማፀናለን። ተባብረን በመቆም ይህንን አይን ያወጣ ግፍ አብረን እንቋቋም።**
**የዘመቻ ጴጥሮስ አስተባባሪ ግብረ ኃይል።** **ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘላለም ትኑር**
**ዳግም የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ እ.አ.አ. ማርች 11 ቀን 2012 ከጧቱ 8:00 ኤ ኤም ጀምሮ**
**በደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል 3010 Earl Pl Ne Washington, DC 20018**

EthioLion.Com